## በጋሞ ጎፋ ዞን የባህላዊና ታሪካዊ /ሰው ሰራሽ/ መስህቦች ቅኝት

በደቡ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት ከሚገኙ ዞኖች የጋሞ ጎፋ ዞን ማራኪ በሆኑ ባህላዊና ታሪካዊ መስህቦች ተጠቃሽ የሆነ የቱሪዝም መዳረሻ ነው፡፡ዞኑ በውስጡ ያቀፋቸው 15 ወረዳዎች በልዩ ልዩ ባህልና ወግ የተሳሰሩ የአምስት ብሔረሰቦች ባለቤት ነው፡፡ አንድነታችን ልዩነታችን ልዩነታችን ውበታችን ነው ብሎው የየራሳቸውን ባህል፣ታሪክ፣ ቋንቋና የአኗኗር ዘዴ ያላቸው የጋሞ፣ የጎፋ፣ የዘይሴ፣ የጊዲቾና የኦይዳ ብሔረሰቦች በአንድ ላይ የሚገኙበት ማራኪ ዞን በመሆኑ ለየት ያደርገዋል፡፡

በዞኑ ከሚገኙ የቱሪስት እይታን ከሚስቡ ባህላዊና ታሪካዊ / ሰው ሰራሽ/ መስህቦች መካከል፡-

- የዶርዜ ባህላዊ መንደር /የሽማ ሥራና የቤት አሠራር/
- የዶርዜ የመስቀል በዓል አከባበር
- የጊሬና የሶፌ ፌስቲቫል
- የጨዩ መስቀል በዓል አከባበር
- የኤሊ ቅዱስ ገብርኤል ገዳም
- የብርብር ማርያም ቤ/ክርስቲያን
- የቦረዳ ሚካኤል ገዳም
- የበሌ መሰላል
- የኩርሻ የጦርነት ሜዳ
- የደንዲሶ ዋሻ እና የመሳሰሉ ይገኙበታል፣

**1.የዞኑ ማራኪ ባህላዊ መስህቦች፡-**

### ሀ/ <u>የዶርዜ ባህላዊ መንደር</u>

የዶርዜ መንደር በ11 ቀበሌዎች የተከፈለ ሲሆን ዶርዜ ሂርጾ፣ ዶርዜ ሃይዞ፣ ዶርዜ አይራ፣ ዶርዜ ላካ፣ ዶርዜ አማራና ቦዶ፣ ዶርዜ ሆሎአና ዶርዜ ጎዲዬ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ዶርዜ በአጠቃላይ ከባህር ወለል በላይ 2000-2800ሜ ከፍታ ያለው ሲሆን ከአርባ ምንጭ 30 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ አከባቢው በዋናነት የሚታወቀው በሽማ ሥራና በባህላዊ የቤት አወቃቀርሩ ነው፡፡ በተጨማሪም የዶርዜ መንደር የሚታወቀው የተለያዩ ማራኪ ትርዒቶች በሚታዩበት የመስቀል በዓል አከባበር ነው፡፡ ይህን ተደናቂ በዓል ከምንም በላይ ልዩ የሚያደርገው ከ3000 በላይ የቀንድ ከብቶች በአንድ የተወሰነ ቦታ የሚታረዱበትና በርካታ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ቱሪስቶች የሚጎርፉበት ሥፍራ በመሆኑ ነው፡፡ በተለያዩ ሥራ ምክንያት ራቅ ወዳለ ሥፍራ የሄዱ የአካባቢው ተወላጆች ይህን በዓል ለማክበር መመለሳቸው በዓሉን ይበልጥ ደማቅ ያደርገዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የዶርዜ ማህበረሰብ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከሚታወቅባቸው የእደ ጥበብ ውጤቶች እንደነጠላ፣ ጋቢ ቡሉኮ እንዲሁም የጋሞ ብሔረሰብ መለያ በሆነው ድንጉዛ አልባሳትን በማምረት ይታወቃል፡፡ ይህን የዕደ ጥበብ ሥራ ለማየትም ሆነ የዶርዜ አካባቢ ባህላዊ መንደር ለመጎብኘት በርካታ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ወደ አካባቢው ያለማቋረጥ ይፈሳሉ፡፡

### *ባህላዊ የሽማ ሥራ*

የጋሞ ብሔረሰብ አባል የሆነው ዶርዜ ማህበረሰብ በሽማ ሥራው በሀገር አቀፍ ደረጃ ይታወቃል፡፡ የሽማ ሥራ ውጤት የሆኑት ነጠላ፣ ጋቢ፣ ቡሉኮ እንዲሁም ሌሎት የዕደ ጥበብ ውጤቶች እንደተጠበቁ ሆነው በተለይም የጋሞ ብሔረሰብ ባህላዊ ልብስና **ድንጉዛ** በመባል የሚታወቀውን ባለደማቅ ቀለም ልብስ የዶርዜ ማህበረሰብ የእጅ ጥበብ ውጤት ነው፡፡ ይህንን ደማቅና ማራኪ ባህላዊ ልብስ በደቡብ ውስጥ የሚገኙ ሌሎችም ብሔረሰቦች የሚጠቀሙት ሲሆን ዋናው የጥበቡ ባለቤት ግን የ**ጋሞ ብሔረሰብ** ነው፡፡ ይህንን የዕደ ጥበብ ሥራና አጠቃላይ የዶርዜን አካባቢ ባህላዊ መንደር በርካታ የውጭ ሀገርና የሀገር ውስጥ ቱሪስቶች ይጎበኙታል፡፡

### *የቤት አሠራር፡-*





ሁሉም አካሉ ቀርከሃ የሆነ የጎጆ ቤት አሠራር ባህል አንዱ የዶርዜ መስህብ ሲሆን የቤቱ አካል ማለትም ግድግዳው፣ ጣሪያው፣ ክዳኑ፣ መዝጊያው ምሶሶውና ማሠሪያው ወዘተ ከቀርከሃ መሆኑ የተለየ እይታን የሚስብ ነው፡፡ የዶረዜ አርሶ አደር በግቢው ከ3-5 ጎጆ ቤቶች ያሉት ሲሆን እነዚህም እልፍኝ ወይም የእንግዳ መቀበያ፣ መኖሪያ ቤት የምግብ ማብሰያ፣ የዕቃ ቤትና የእንስሳት ማደሪያ ቤት ወዘተ በመባል ይከፋፈላሉ፡፡ ብዙ ጎጆዎች በእንሰትና በቀርከሃ አጥር ተከበው አንድ መንደር የሚመስለውን የአንድ አባወራ ቤት ግቢ ማየት ሌላው አስደሳች ትዕይንትና በቱሪስቶች ተወዳጅነትን ያተረፈ መስህብ ነው፡፡







ጨዩ አከባቢ የመስቀል በዓል አከባበር

# የጋሞ ጎፋ ዞን
# ቱሪዝምና ፖርኮች ልማትና አጠቃቀም ዋና የሥራ ሂደት

ስልክ ቁጥር ☏ 046-881-2046
ፖ.ሣ.ቁጥር 🖂 70

**መስከረም 2006** ዓ.ም
<u>አ/ምንጭ</u>

***የጋሞ መስቀል በዓል አከባበር በዶርዜ አከባቢ***

መስቀል በዓል በጋሞ **ብሔረሰብም** ሆነ በሌሎች በዞኑ ባሉ ብሔረሰቦች የተለመደ በዓል ነው፡፡ ጋሞዎች የመስቀል በዓልን ልዩ ዝግጅት አድርገው የሚያከብሩ **ሲሆን** ለዚህ በዓል ሲባል አስቀድሞ ገንዘብ ማጠራቀም፣ የእህል አይነቶችን ገዝቶ ማስቀመጥና የቤት እነስሳት መኖ ማዘጋጀት የተለመደ ነው፡፡ **በጨንቻ ወረዳ ዶርዜ አካባቢ የሚከበረውን** ተደናቂ **የመስቀል በዓል** ከምንም በላይ ልዩ የሚያደርገው በወቅቱ ከ3000 በላይ የቀንድ ከብቶች አንድ ላይ በተወሰነ ቦታ መታረዳቸው ነው፡፡ በአጠቃላይ ይህንን ትዕይንት ለማየት በርካታ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ኘሮግራም ይዘው ይመጣሉ፡፡ በተለያየ ሥራ ምክንያት ራቅ ወዳለ ስፍራ የሄዱ የአካባቢው ተወላጆች ይህን በዓል ለማክበር ወደ ትውልድ ቄያቸው መመለሳቸው በዓሉን ደማቅ ያደርገዋል፡፡



*የመስቀል እርድ በዶርዜ*



### የሶፌ በዓል አከባበር

የሶፌና የፂሬ በዓል አከባበር አብዛኛው የጋሞ ብሔረሰብ በሚገኝበት አከባቢዎች በሰፊውና በደማቅ ሁኔታ የሚከበር ሲሆን ከመስቀል በዓል ጋር ተያይዞ የሚመጣ ነው፡፡ ይህ በዓል ከመከበሩ ከ2 ወር በፊት ቀድሞው ጋብቻቸውን የፈፀሙ የአካባቢው ሙሽሮች በናፍቆትና በጉጉት የሚጠብቁት በዓል ስለሆነ እራሳቸውን በትዳር ውስጥ ምን ያህል እንደተስማማቸውና ውብ ገጽታቸውን ለማሳየት በበዓሉ በባህላዊ አለባበስ፣ አጋጌጥ እና የፀጉር አሠራር ተውበው የሚታዩበት ነው፡፡ በዓሉን በተለያዩ ባህላዊ ዘፈንና ጭፈራ ትዕይንት የታጀበ ከመሆኑ የተነሣ የብዙሃንን ቀልብ ይስባል፡፡ ይህ በዓል የሙሽሮች የቁንጅና ውድድር የሚካሄድበት ወቅትም



*የዲታ ሙሽሮች በሶፌ ወቅት*

ጭምር ነው፡

#### የጮዬ መስቀል በዓል አከባበር

ጮዬ በዳራማሎ ወረዳ የሚገኝ ቀበሌ ሲሆን ከዳራማሎ ርዕሰ ከተማ ዋጫ በ31 ኪ.ሜ ርቀት እና ከአ/ምንጭ በ197 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ የጮዬ መስቀል በዞኑም ሆነ በሀገራችን ለየት ባለ መልኩ የሚከበር እጅግ ማራኪ የመስቀል በአል አከባበር ሲሆን ዓይነተኛ የቱሪስት መዳረሻ ነው፡፡

የመስቀል በዓሉ የሚከበረው እንደ አብዛኛው የሀገራችን ክፍል መስከረም ወርን ጠብቆ ሳይሆን ከህዳር እስከ ታህሳስ ወር በአከባቢው ባህላዊ የቀን አቆጣጠር ሥርዓትና በድንቅ ትዕይንት የታጀበ በመሆኑ ለየት ያደርገዋል፡፡ በዓሉን ለማክበር ከ 7 አጎራባች ቀበሌያት የመጡ ታዳሚዎች ከባህላዊ አልባሳታቸው ጋር ደምቀው የሚታደሙበትና በማራኪ የፈረስ ግልቢያ በዓሉን ያደምቁታል፡፡ የመስቀሉ ቀን የሚወሰነው በአከባቢው ህብረተሰብ የተመረጡ ሁዱጋዎች (የሀገር ሽማግሌዎች/ ባላባቶች) ሲሆን የአከባቢውን የመኸር ወቅት ምክንያት በማድረግ የጥጋብና የደስታ በዓል እንዲሆን እንዲሁም ለአከባቢው ሰላም መልካም ምኞትን በመመኘትና ለህብረተሰቡ አንድነት፤ ፍቅርና ጤና በመፀለይ እና ቤት ያፈራውን ቅንጬ፤ቡላ፤ወተት፤አይብና በርካታ ቁጥር ያላቸው በሬ ዎች ታርደው በአንድነት በመመገብ ይከበራል፡፡ይህ ብቻ አይደለም ፤በአከባበሩ ሥርዓት ማራኪ የሆነው የሶፌ ስርዓት የሚታይበት ከመሆኑ በላይ ወጣቶች በባህላዊ ጭፈራና ዘፈን በዓሉን የሚያደምቁበት ልዩ ትዕይንት ነው፡፡



የጮዬ መስቀል በዓል አከባበር

### የዞኑ ማራኪ ታሪካዊ መስህቦች

#### ሀ/ የኤሊ ቅዱስ ገብረኤል ገዳም

የኤሊ ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ከአ/ምንጭ 65 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ ገዳሙ በዳራማሎ ወረዳ የሚገኝ ሲሆን ከተለያዩ አቅጣጫ የሚመጡ በብዙ መቶ ሺ የሚቆጠሩ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች በየዓመቱ ታህሳስ 19 እና ሐምሌ 19 ቀን ጠብቀው ሥርዓተ አምልኮ የሚፈጽሙበት ገዳም ነው፡፡ ከ400 ዓመት በላይ ዕድሜ ያለው ይህ ቅዱስ ገዳም በውስጡ የወርቅ ቅብ መስቀል፣ የብር መቋሚያ፣ የዝሆን ጥርስ፣ የሰጎን እንቁላል፣ የብራና ላይ ጽሁፍና ሌሎች በርካታ ጥንታዊ ንዋዬ ቅዱሳን ይገኙበታል፡፡



#### ለ/ የብርብር ማሪያም ቤ/ክርስቲያን

የብርብር ቅድስት ማርያም ገዳም በኢትዮጵያ ከሚገኙ ቀደምት ገዳማት አንደዷ እንደሆነች ከትውፊት የተገኙ መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ አናኒያንና አዛሪያን የሚበሉ ሊቀነ ካህናት ታቦት ጽላቱን ከኢየሩሳሌም ቀይ ባህርን አሻግረው ከአክሱም ታቦት ፅዮን ጋር እንዳመጧት ይነገራል፡፡

በ1440 ዓ.ም አፄ ዘርዓ- ያዕቆብ ከትግራይ፣ በ1530 ዓ.ም አፄ ልብነ -ድንግል እንዲሁም በ1961 ዓ.ም ግርማዊነታቸው ቀዳማዊ አፄ ኃይሌ ሥላሴ ወደ ቤ/ክርስቲያኒቷ በመምጣት ተሳልመውና የተለያዩ ንዋየ ቅድሳትን ድጋፍ እንደሰጡ የሚነገርላት የብርብር ማርያም ቤ/ክርስቲያን ከዞኑ አ/ምንጭ ከተማ 67 ኪ.ሜ ርቀት እንዲሁም ከምዕራብ አባያ ዋና ከተማ ብርብር በ82 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ ይህ ቅዱስ ስፍራ ከዞኑ ከተለያዩ አቅጣጫ የሚመጡ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ምዕመናን አዘውትረው ሕዝበ ፀሎት የሚያደርሱበትና ከተለያዩ በሽታዎች የእምነት ፈውስ የሚያገኙበት ቦታ ነው፡፡ ቤተክርስቲያኗም ጥንታዊና ታሪካዊ የሆነ በርካታ ነዋየ ቅድስትና መንፈሳዊ ቅርሶችን ያቀፈች ገዳም በመሆኗ የብዙ ቱሪስቶችን ቀልብ እንደሚስብ ይታመናል፡፡



#### የበሌ ቶንጎላ መሰላል

የበሌ ቶንጋላ መሰላል በታሪካዊነቱና በሰው ሰራሽ መስህብነቱ ተጠቃሽ ሲሆን ከአርባ ምንጭ ከተማ በ36 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በጨንቻ ወረዳ በሌ በሚባል ቀበሌ ይገኛል፡፡ ይህ መሰላል ረጅም ዕድሜ ያስቆጠረ ሰው ሰራሽ መሰላል ሲሆን ሁለት በተለያዩ አቅጣጫና ርቀት ላይ የሚገኙ የቁርጼና የጨዮ ንኡስ ቀበሌዎችን የሚያገናኝ የ30 ሜትር ርዝማኔ ያለው ከሀበሻ ጥድ የተሰራ ድልድይ መሆኑ ለየት ያደርገዋል፡፡ ቀድሞ ብዙ ርቀት ተጉዘው ይገናኙ የነበሩ የሁለቱ ንዑስ ቀበሌያት ነዋሪዎች መሰላሉ በፈጠረላቸው አቋራጭ (Short path) ተጠቃሚ በመሆናቸው ጠንካራ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት እንዲኖራቸው ረድቷል፡፡